4127 Redwood
Oakland, CA 94619
(510) 530-3681

NO፣ 170/08
Date 05/23/2008

# ስለ ኢትዮጵያ ወቅታዊ አሳሳቢ ጉዳዮች በስደት ላይ ከሚገኘው ሕጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ የተሰጠ መግለጫ፤

በስደት ላይ ያለው ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ በዋሽንግተን ዲሲ ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል ፳፭ኛውን መደበኛ ስብሰባ ከግንቦት ፲፫ ቀን ፳፻ ዓ/ም ጀምሮ እስከ ግንቦት ፲፭ ቀን ፳፻ ዓ/ም አካሂዷል።

ቅዱስ ሲኖዶስ በጉባኤው፥ ቤተ ክርስቲያኒቱ በምታከናውናቸው ተግባራት ላይ ሰፊና ጥልቅ ውይይት አድርጓል። በስብከተ ወንጌል፥ በገዳማትና አድባራት ይዞታ፥ አዲስ በተሾሙት ጳጳሳት የሥራ እንስቃሴ፥በኢትዮጵያ እየተሰራጨ ባለው የቅዱስ ሲኖዶስ ራዲዮ የሰንበት ትምህርት ቤቶች እንቅስቃሴና በመጨረሻም እየተካሄደ ስላለው የሰላም እና የእርቅ እንቅስቃሴ ሪፖርት በመስማት በየመምሪያዎቹ ሊከናወኑ ስለሚገባቸው ተግባራት የተለያዩ ውሳኔዎችን አስተላልፎአል።

እንደተለመደው ሲኖዶሱ በትኩረት ከተወያየባቸው ዓበይት ጉዳዮች መካከል የቅድስት ሀገራችን ኢትዮጵያ ሁኔታ ቅድሚያ ተሰጥቶት ነበር። ስለ ሀገራችን የምንሰማው ዜና ሁሉ ከዕለት ወደ ዕለት የሕዝቡን ኑሮ የሚያዳክም የመኖር ተስፋውንም የሚያጨልም እንደሆነ ተገንዝበናል። ፍትሕ ርትዕ የጠፋበት ማን አለብኝነት አስተዳደር በመንሰራፋቱ ከዛሬ ነገ ይሻላል የሚባል የተስፋ ጭላንጭል አይታይም።

ኢሕአዴግ በደቡብና በምዕራብ ኢትዮጵያ ከሱዳን ጋር የሚዋሰኑትን ክልሎች፥ አንድ ሺህ ስድስት መቶ ኪሎ ሜትር ያካተተ የአገራችን ዳር ድንበር ለሱዳን አሳልፎ በመስጠት ላይ የጀመረው ግልጥ ሴራ በአካባቢው ነዋሪ ሕዝብ የተጋለጠ በመሆኑ፥ደባው ይፋ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ይህን ያልተቀበሉ የአካባቢው ነዋሪዎችና በልማት ሥራ ላይ የተሰማሩ በርከት ያሉ ወገኖቻችን በሱዳን እስር ቤት ይገኛሉ፤ ንብረታቸው ተቃጥሏል። ከኑሯቸው ተፈናቅለዋል፥ከፍተኛ ገንዘብ እንዲከፍሉ ወይም በሁለት ዓመት እስራት እንዲቀጡ እንደ ተበየነባቸው ከራሳቸው አንደበትና በቅርቡ ከወጡ የመገናኛ ብዙኃን መረጃዎች ለመረዳት ችለናል።

በመሠረቱ አሁን በሱዳን ድንበር በኩል ድንገት ያገረሸው የወሰን ይገባኛል ጥያቄ ቀደ
ም ሲል በአፄ ምኒልክ እና በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በተደጋጋሚ የተነሣና
ብዙ መጻጻፍ የተደረገበት ሲሆን፥በተለይ በደርግ ዘመነ መንግሥት ምርጥ ኢትዮጵያው
ያን ምሁራንን ያካተተ ኮሚቴ ተቋቁሞ ታሪካዊ ሰነዶችን፥ነባር ካርታዎችንና ዓለም አቀ
ፍ የስምምነት ውሎችን መሠረት ያደረገ፥ የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያስከብር አስተማ
ማኝ ጥናት ለመንግሥት የቀረበ መሆኑ የተረጋገጠ ነው። መንግሥት የሕዝብ ተጠሪ እን
ደመሆኑ መጠን ለሀገር ሉዓላዊነትና ለወሰን መከበር ኢትዮጵያን የሚጠቅመውን ጥናት
በሥራ ላይ ለማዋል መሞከር የመሪዎች ኃላፊነት ነበር። በየጊዜው የተነሡ የኢትዮጵያ
መሪዎች ሁሉ በወሰናቸው የተደራደሩበት ወይም በሀገራቸው ሉዓላዊነት የሚነሱ ጥያቄ
ዎችን ችላ ያሉበት ጊዜ አልነበረም።

የሕዝቡን መብት ረግጦ በባለሙያዎች የተጠናውን ጥናት ወደጎን በማድረግ የኢትዮጵ
ያን ሉዓላዊነት ያስደፈረና የዳር ድንበሩን ለም መሬት ቆርሶ ለባዕድ በመስጠት በወገኖ
ቹ ላይ ግፍ በመፈጸም የሚገኝ አገዛዝ ቢኖር በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ኢሕአዴግ ብ
ቻ እንደሆነ በተደጋጋሚ ተረጋግጦአል።

ይልቁንም ሀገራችን በደረሰባት የኢኮኖሚ ክስረት ምክንያት ሕዝባችን በአገር ውስጥ
የተከሰተውን መቋጫ የሌለው የኑሮ ውድነት መቋቋም አቅቶት በረሃብ አለንጋ እየተገረ
ፈ አቅመ ቢስ በሆነበት በዚህ ወቅት እንዲህ ዓይነቱ በሉዓላዊነታችን ላይ ያነጣጠረና
ለከፋ ስደት የሚዳርግ ችግር መከሰቱ ለኢትዮጵያውያን ሁሉ ከባድ ፈተና እንደሆነ
ማንም ሊዘነጋው አይገባም።

በኢህአዴግ የአገዛዝ ዘመን ኢትዮጵያውያን በሀገራቸው ወሰን ላይ ያላቸው ስሜት ምን
ያህል እንደተጎዳ፥ ከኤርትራ ጋር በተደረገው ጦርነት የነበረውን ሁኔታ ማስታወስ ብቻ
በቂ ነው። ያ ጦርነት ያስከፈለው መሥዋዕትነትና ጥሎት ያለፈው ጠባሳ ገና ቁስሉ ሳይ
ደርቅ፥አሁን እንደገና ታላላቆቹ የሀገራችን መሪዎች አፄ ቴዎድሮስና ጀግናው ኢትዮጵ
ያዊ ሰማዕት አፄ ዮሐንስ የሞቱበትን በደም የተከበረውን የሀገራችን ድንበር ለባዕድ አ
ሳልፎ መስጠት ፍጹም ይቅርታ የማይገኝለት በሀገር ላይ የተፈጸመ ክህደት በመሆኑ ቅ
ዱስ ሲኖዶስ ይህንን ድርጊት አጥብቆ ያወግዛል።

በድርቡሽም ጭፍን ወረራ ካህናትና አብያተ ክርስቲያናት ከነቅርሳቸው መውደማቸውን
የሚያስታውሰው በከባድ ኃዘን መሆኑን እየገለጠ፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ
ክርስቲያን ሕዝቦቿን ለሀገር ዳር ድንበር መጠበቅ ስትመራ የኖረች እንደመሆኑዋ መጠን
ቅዱስ ሲኖዶስ በጉዳዩ ላይ በጥልቀት ከተወያየ በኋላ የሚከተለውን የአቋም መግለጫ
አውጥቶአል።

ሀ. አሁን በአካባቢው ነዋሪዎች ላይ እየተፈጸመ ያለው ግፍ እንዲቆም፤ የተፈና
ቀሉት ወደ ቦታቸው እንዲመለሱ፤ በዚህም ምክንያት የታሰሩ እንዲፈቱና ክስ የተመሠ
ረተባቸውም ነጻ እንዲለቀቁ በማድረግ ጉዳዩ የሚመለከተው ክፍል ያለበትን ኃላፊነት
እንዲወጣ ቅዱስ ሲኖዶስ ያሳስባል።

ለ. የሱዳን መንግሥት አሁን እየፈጸመ ያለው ትንኮሳ ምሥራቅ አፍሪካን ሊያና
ውጥ የሚችል ብጥብጥ እንደሚፈጥር ተገንዝቦ ከኢህአዴግ የተሰጠውን አጉል ተስፋ

ወደ ጎን በመተው የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት እንዲያከብር ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን ያስተላልፋል።

ሐ. መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ « ዳሩ ሲደፈር መሐሉ ዳር ይሆናል» የሚለውን የአበው ብሒል በመገንዘብ ለዳር ድንበሩ መደፈር እየተዋደቀ ካለው የድንበሩ አካባቢ ሕዝብ ጎን እንዲቆም፤ የተፈናቀሉትን በመርዳትና መልሶ በማቋቋም አጋርነቱን እንዲያሳይ ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን ያስተላልፋል። የበኩሉንም አስተዋፅዖ ያደርጋል።

መ. ከዚህም ጋር ከአብደራፊ እስከ አሰብ ከሌሎች ክፍለ ሀገራት ተቆርሶ ወደ ትግራይ በጉልበት የተከለለውም መሬት እንደ ቅድመ ሥሪቱና ባሕሉ ተከብሮ የሀገሬው ሕዝብ በሰላምና በፍቅር እንዲኖር እያሳሰብን፤ ይህ ሳይሆን ቀርቶ በማን አለብኝነት ለሚፈጸመው በደል ሕዝቡ የሚያደርገውን ተቃውሞ ያለማወላወል እንደግፋለን።

ለሁሉም መሠረቱ ሰላም እንደሆነ « አስቀድማችሁ የሀገርን ሰላሟን ፈልጉ በማለት ቅዱስ መጽሐፋችን ያዛል»። ቅዱስ ሲኖዶስም ይህን ለመፈጸም እና ለማስፈጸም ኃላፊነት እንዳለበት በተደጋጋሚ ገልጦአል። ከኢህአዴግ ጋር ፊቱን የተዟዟረው የኢትዮጵያ ሕዝብ እርቅ ሰላምን አግኝቶ፥ኢህአዴግም ከሕዝቡ ጋር ታርቆ፥አገሩን ለመታደግና ልማቱን ለማሳደግ እንዲችል ሁሉን አቀፍ የሆነ እርቅ እንዲፈጸም ቅዱስ ሲኖዶስ ይጸልያል። አሁንም በድጋሚ በሩን ከፍቶ እጁን ዘርግቶ ለኢትዮጵያ ሰላም ለቤተ ክርስቲያን ደኅንነት ሲባል ሥርዓተ ቀኖናው ተጠብቆ፥እርቅ ሰላም እንዲፈጸም የተቻለውን ሁሉ ጥረት ያደርጋል።

እግዚአብሔር አምላክ ለሀገራችን ሰላምን፥ለሕዝባችን ፍቅር አንድነትን ያድልልን።
አሜን።

በስደት ያለው ሕጋዊ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ።

ዋሽንግተን ዲሲ ግንቦት ፲፭ ቀን ፳፻ ዓ/ም